የ ድ ሬ ዳ ዋ   አ ስ ተ ዳ ደ ር

# ድ ሬ  ነ ጋ ሪ ት  ጋ ዜ ጣ

# D I R E  N E G A R I T  G A Z E T A

## OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION

2ኛ ዓመት ቁጥር 40
ትሬቴ□ ሰኔ 1 ቀን 2007 ዓ/ም

በትሬቴ□ አስተዳደር
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 40
DIRE DAWA 8th June 2015

## አዋጅ ቁጥር 40 /2007

**የድሬዳዋ አስተዳደር የአስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

የድሬዳዋ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 16/2003 ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የድሬደዋ አስተዳደር ምክር ቤት በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ‹‹ሀ›› በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቶአል፡፡

## PROCLAMATION No 40 /2015

**APROCLAMATION TO AMEND THE DEFINITION OF POWERS AND DUTIES AND RE-ESTABLISHMENT OF THE EXECUTIVE AND MUNICIPAL SERVICE ORGANS OF DIRE DAWA ADMINISTRATION.**

WHEREAS, it has found necessary to amend the definition of powers and duties and Re-establishment of the executive and municipal

service organs of the Dire Dawa Adminstration proclamation No. 16/2010;

NOW, THERFORE, in accordance with Article 12 (1) (A) of the Dire Dawa Administration charter proclamation No. 416/2004, the Dire Dawa Administration council, is hereby proclaimed as follows.

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ‹‹የድሬዳዋ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 40/2007›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ማሻሻያ

የድሬዳዋ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 16/2003 ዓ/ም እንደሚከተለው ተሻሽሎአል፡፡

1. በአዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (9) ስር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (10) እና (11) ተጨምረዋል፣

   ‹‹10›› የመሬት ልማት እና ማናጅመንት ቢሮ፣

   ‹‹11›› የኮንስትራክሽን እና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ቢሮ
2. የአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (10) ተሰርዞአል፡፡
3. የአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) ተሰርዞ ፊደል ተራ (ሐ) እና (መ) እንደቅደም ተከተላቸው ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) ሆነዋል፡፡
4. የአዋጁ አንቀጽ 12 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 12 ተተክቶአል፣

   ‹‹12›› **የስፖርት ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር**

   ኮሚሽኑ በድሬዳዋ አስተዳደር የስፖርት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 22/2004 ላይ የተገለፀው ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## 1. Short Title

This proclamation may be cited as the "Definition of powers and duties and Re-establishment of the executive and Municipal Service organs of the Dire Dawa Administration (Amendment) Proclamation No, 40 /2015."

## 2. Amendment

The Definition of power and Duties the executive and municipal service organs of the Dire Dawa Administration Proclamation No,16/2010 is here by amended as follows.

1. The following new sub-Article (10) and (11) are added under sub-Article (9) of Article 4 of the proclamation.

   "10". Land Development and Management Bureau.

8. Provide support for the establishment of community participation in every locality, so as to bring land and city development which centered community participation.
9. Carryout plan consistency activities.
10. Implement construction proclamation.
11. Give full leadership to billboards installed in the city and advertisements posted on buildings in the city, prepare payment scale and execute the same.
12. Administer by requesting recurrent and capital budget which is decisive for the whole sector.
13. Recruit, administer and dismiss the needed man power in accordance with the structure and directive of human resource management.
14. Undertake other activities necessary for the fulfillement of its objectives.

34. **powers and duties of accumulated work's and possession administration transitional period service project office**

The office shall have powers and duties indicated in the Dire Dawa administration Accummulated work's and possession administration transitional period service

‹‹34›› **የውዝፍ ሥራዎች እና የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ መስተንግዶ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር**

ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ በድሬዳዋ አስተዳደር የውዝፍ ሥራዎች እና የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ መስተንግዶ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 32 /2006 የተገለፀው ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

‹‹35›› **የተቀናጀ የመሬትና መሬት ነክ መረጃ ሥርዓት ዝርጋታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ሥልጠና ተግባር**

ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ በድሬዳዋ አስተዳደር የተቀናጀ የመሬት እና መሬት ነክ መረጃ ሥርኣት ዝርጋታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 31/2006 ተገለፀው ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

‹‹36›› **የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው በድሬዳዋ አስተዳደር የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 39/2007 የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

submit the same for the cabinet and execute upon approval;

**15.** Cause the preparation of service delivery standards and directions and submit to the cabinet, execute it upon approval, ensure the rendering of facilitated fruitful and fair municipal service;

**16.** Generate policy ideas and legislative draft concerning municipal service and submit it to the cabinet, and execute the same upon approval;

**17.** Enforce decisions concerning municipal service;

**18.** Entertain complaints by the residents regarding municipal service and respond to the claims as much as possible;

**19.** Facilitate conditions to give sustainable solutions to the causes or sources of the complaints by causing the undertaking of separate study on it;

**20.** Establish and lead management committee consisted of departments and institutions established under it;

**21.** Function firmly in corberation with appropriate organs and residents of the city;

**22.** Carry other activities to meet its objectives;

6. የአዋጁ ክፍል አራት ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ክፍል አራት ተተክቶአል፤

**ክፍል አራት**

**ስለኮንስትራክሽን እና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት**

2. እያንዳንዱ የኮንስትራክሽን እና የማዘጋጃ ቤታዊ አልግሎት አካል የራሱ የሆነ የሥራ ክፍሎች እና ሠራተኞች ይኖሩታል፣

**6.** Part four of the proclamation is repealed and replaced by the following new part for.

**PART FOUR**

**ORGANS OF CONSTRUCTION AND MUNICIPAL SERVICE**

7. የአዋጁ አንቀጽ 37 እና 38 ተሰርዘዋል፣

**7.** Article 37 and 38 of the proclamation is deleted

8. የአዋጁ የቀድሞ አንቀጽ 33, 34, 35, 36, 39, 40,41,42 እና 43, እንደቅደም ተከተላቸው 38,39,40,41,39,42,43,44,45 እና 46 ሆነዋል፣

**8.** The Formes Articles 33,34,35,36,39,40,41,42 and 43 of the proclamation are re-numbered as Article 38,39,40,41,39,42,43,44,45 and 46 respectively.

9. የአዋጁ አንቀጽ 38 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 38 ተተክቶአል፤

‹‹38›› **የኮንስትራንሽን እና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት መቋቋም፤**

1. የሚከተሉት የኮንስትራክሽን እና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት ህጋዊ ሰውነት በማግኘት ተቋቁመዋል፣

   ሀ. የጽዳት፣ ውበትና የመናፈሻ ልማት ኤጀንሲ፤

   ለ. የቄራ አገልግሎት ድርጅት፣

   ሐ. የቤቶች ልማት ማናጅመንት እና ኮንስ ትራክሽን ኤጀንሲ፣

**9.** Article 35 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Article 35.

**"38". Establishment of Organs of construction and Muncipal service**

1. The Construction and municipal service organs of the administration that have legal personality established as follows;

   a. Sanitation, Beautification and parks development Agence;

b. Abattoir service;

c. Housing development Management and construction Agency;

2. Each construction and municipal service organ shall have appropriate work units and employees;

3. የኮንስትራክን እና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት እንዳስፈላጊነቱና አመቺነቱ እንደ ህግ አገልግሎት እና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶችን በጋራ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚያፀድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት ይወሰናል፡፡

10. የአዋጁ አንቀጽ 39 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 39ተተክቶአል፤

‹‹39››በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት የኮንስትራክሽን እና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት ተጠሪነታቸው ለኮንስትራክሽን እና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ቢሮ ይሆናል፡፡

11. የአዋጁ አንቀጽ 40 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 40 ተተክቶአል፤

‹‹40›› <u>ስለሌሎች የኮንስትራክሽን እና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት</u>፤

1. የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፤
2. የመንገዶች ባለስልጣን፤ ፤
3. የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት
4. የደንብ ማስከበርና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት ተጠሪነት ለኮንስትራክሽን እና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ቢሮ ሆኖ ቀደም ብለው በተቋቋሙባቸው ህግ በተደነገገው መሠረት ስራቸውን ይቀጥላሉ፤

12. ከአዋጁ አንቀጽ 46 ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጽ 46 ተጨምሮአል፡፡

3. The construction and municipal service organ may be used the supporting staff services commonly such instance of legal services. The details of the organizational structures shall be approved by the cabinet.

**10.** Article 39 of the proclamation is repealed and replaced by the following new Article 39. amended as follows.

"39" in this proclamation article 39 sub article (1) of the stated construction and municipal service organs shall accountable to construction and municipal service Bureau.

**11.** Article 40 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Article 40.

**"40" <u>For others construction and municipal service organs</u>.**

1. Water and sewerage Authority;
2. Roods Authority; and
3. Housing Development project office
4. Code enforcement and vital registration office are accountable to construction and municipal service Bureau. And then shall continue their function in accordance with legislation establishing them.

**12.** The following new article 46 is added after article 46 of the proclamation.

**‹‹46››. <u>የቤቶች ልማት ማናጅመንት እና ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር</u>**

**ኤጀንሲው፡-**

1. ዘርፉ የሚመራበትንና እንዲሁም ቤቶችን የሚመለከቱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አ□ቓፀቶ □ቀርባል፣ ሲፀድቁም ተፈፃሚነታቸውን ያረጋግጣል፣
2. አስፈላጊ ሲሆን በአስተዳደሩ በጀት ለሚገነቡ ግንባታዎች የሚያገለግሉ ውሎችና ውሎች ስለሚይዟቸው የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች ዝርዝር የቴክኒክ መመርያ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር በመመካከር በማዘጋጀት በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
3. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዕድገት ከግብዓት አቅርቦት ጋር መጣጣም እንዲችል የግንባታ ግብዓት አምራቾችና አከፋፋዮች በጥራትና በብዛት እንዲያቀርቡ ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፣ ይደግፋል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣
4. የኮንስትራክሽን ዘርፍ የመረጃ መረብና ማዕከል እንዲኖር በማድረግ ወቅታዊ የዘርፉ መረጃዎች ተሰብስበው፣ ተመዝግበውና መረጃዎች ተተንትነው የልማት አቅጣጫዎችን መጠቆም በሚችሉ አግባብ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፣

**"46" <u>Powers and Duties of Housing Development Management and construction Agency</u>**

The Agency Shall :-

1. Prepare and submit proclamations, regulations and directives to guide the sector and the houses as well ensure their enforcement upon approval;
2. When necessary, prepare detailed technical directive in consultation with finance and economic development bureau regarding terms and conditions of contract for

buildings constructed by budget of the administration and execute the same;

3. Device a strategy for producers and distributors of construction input to provide in quality and quantity, to make the growth of construction industry compatible with input supply;

4. Ensure the collection, registration and interpretation of updated information of the sector in a manner to indicate development direction by causing the establishment of information network center for the construction sector;

5. በመንግስትና በሌሎች አካላት ለሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የመሠረተ ልማት አቅርቦት እንዲሟላ የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፣

6. ለቤት ልማት የሚያስፈልግ የመሬት፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦት በዘላቂነት የሚረጋገጥበትንና እንዲሁም የፋይናንስ አማራጭ በማጥናት ለአፈፃፀም የሚረዳ የአሰራር ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣ በአፈፃፀም ይደግፋል፣

7. ለቤቶች ልማት አጋዥ የሆኑ አማራጭ የግንባታ ግብአቶች እንዲቀርቡ ይደግፋል ያስተባብራል፤እንዳስፈላጊነቱ ወጭ ቆጣቢ የግንባታ እቃ የሚያመርቱ ፋብሪካዎችንና ተጓዳኝ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ያቋቁማል፣አፈፃፀማቸውን ይገመግማል፡፡

8. በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የተወረሱና አስተዳደሩ የገነባቸውንና የሚገነባቸውን ቤቶች ያስተዳድራል፤ በሕግ አግባብ ለተጠቃሚው አገልግሎት መዋላቸውንና አዲስ የሚገነቡ ቤቶችም በደንቡ መሠረት ለተጠቃሚዎች መተላለፋቸውን ያረጋግጣል፣

9. የመኖሪያ ቤት እጥረት ማቃለል እንዲቻል የተለያዩ አማራጮችን ያስጠናል፤ እንዲሁም በአካባቢ ማቴሪያሎች የሚገነቡ ስታንዳርድ ዲዛይኖችን በማዘጋጀት አነስተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸው የከተማው ነዋሪዎች ተገቢ የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ ወጭ ቆጣቢና በዋጋ ተደራሽ ቤቶች በስፋት እንዲገነቡ ያስተባብራል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፣

5. Coordinate concerned bodies for the full provision of inputs of infrastructure for condominium built by government and other organs;

6. Cause the enactment of working system for the sustainable provision of land and infrastructure necessary for housing development, by undertaking study on financial alternative as well, support its enforcement;

7. Support and coordinate the provision of optional construction inputs which are

supportive to housing development, establish cost effective construction material producing industries and institutions that carry out other related activities, evaluate their performance;

**8.** Ensure that houses of the administration are serving the consumers in accordance with the law and whether the newly built constructions the transferred to consumers in accordance with the regulation;

**9.** Cause the undertaking of different alternative study so as to reduce shortage of dwelling houses prepare standard designs to be built by domestic materials in and coordinate the construction of quality, standardized, cost effective and affordable houses for low and middle income generating residents of the city and follow up the execution of the same;

10. በአስተዳደሩ በጀት ለሚሰሩ የመኖሪያ ቤቶችና የመንግሥት ህንፃዎች ዲዛይኖች፣ ፕላኖችና የስራ ዝርዝሮች በራስ ኃይል ወይንም በአማካሪ ድርጅት በጥራት እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

11. በአስተዳደሩ የሚገነቡትን የመኖሪያ ቤቶችና ሌሎች የመንግሥት ሕንፃዎች በተገባለት ውል መሠረት የጥራት ደረጃቸው፣ የጊዜና የዋጋ ገደቦች ተጠብቀው መሠራታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

12. ህዝቡ የልማቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ እና ተሳታፊ እንዲሆን ለማድረግ በሚሰሩ ልዩ ልዩ የአካባቢ ልማት ሥራዎች ላይ ድጋፎችን ያደርጋል' የልማት ሥራዎችን አፈፃፀም ይገመግማል፤

13. ለጎርፍ የተጋለጡ የከተማዋን ክፍሎች በተመለከተ የመከላከል ሥራው ያለበትን ደረጃ ይገመግማል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል።

14. የሴክተሩ መደበኛና ካፒታል በጀት ጠይቆ በማስፈቀድ ያስተዳድራል፣

15. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ከቢሮው የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፣

**10.** Cause the preparation of designs, plans and work details for the dwelling house and public institutions to be built by budget of the administration, either by its manpower or by consultancy organizations;

**11.** Cause the formation of monitoring system of the construction of dwelling houses and other public buildings maintaining the quality standard, time and price as per the

concluded contract, follow up and supervise the same;

12. Provide support to community development activities to make the public direct beneficiary and participant of the development and evaluate the performance of community development activities;
13. Evaluate the level of preventing the urban areas exposed to flood, and follow up the execution of the same;
14. Administer by requesting the recurrent and capital budget of the sector;
15. Carryout other activates to be given by the bureau to meet its objectives;

13. ከአዋጅ አንቀጽ 43 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዕስ አንቀጽ 44 ተጨምሮአል፡፡

"44" **የደንብ ማስከበርና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት ስልጣንና ተግባር**

ጽህፈት ቤቱ በድሬዳዋ አስተዳደር የደንብ ማስከበርና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 38/2007 የተገለፀው ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

14. የአዋጁ አንቀጽ 45 ተሰርዟል፤
15. የአዋጁ የቀድሞ አንቀጽ 44, 46, 47, 48, እና 49 እንደቅደም ተከተላቸው 44, 45 46, 47 እና 48 ሆነዋል፡፡
16. የአዋጁ አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ (3) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ (3) ተተክቶአል፡፡

‹‹48››3. የኮንስትራክሽን እና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት የቦርድ ሰብሳቢና አባላት በኮንስትራክሽን እና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ቢሮ ኃላፊ አቅራቢነት በካቢኔው ይሰየማሉ፡፡

17. የአዋጁ አንቀጽ 50 ከንዑስ አንቀጽ (4) ተሰርዞ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) ተጨምረዋል፡፡

‹‹50›› (4) የከተማው ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኮንስትራክሽን እና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ቢሮ ተላልፎአል፤

‹‹50›› (5) የመሬት ልማት እና አስተዳደር ሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለመሬት ልማትና ማናጅመንት ቢሮ ተላልፎአል፡፡

**13. The folloing new article 44 is added after article 43 of the proclamation.**

‹‹44›› <u>powers and duties of code Enforcement and Vital Registration office .</u>

The office shall have powers and duties indicated in the Dire Dawa Administration codde inforcement and Vital Registration office establishment proclamation no 38/2015

**14.** Article 45 of the Proclamation is deleted.

**15**. The Formes Articles 44, 46, 47,48 and 49 of the proclamation are re-numbered as Article 44,45,46,47 and 48 respectively.

**16.** Sub Article (3) of Article 48 of the proclamation is repealed and replaced by the following new Sub-Article (3) of Article 48.

**"48".**3 The chair person and members of the construction and municipal service organs board shall be appointed by the cabinet up on the recommendation of the constitution and municipal service Bureau**;**

**17**. Sub-article (4) of Article 50 of the proclamation is repealed and replaced by the following new Sub-articles (4) and (5);

**"50" (**4) The rights and obligation given to the city manager office hereby transferred to the construction and municipal service Bureau

"50" (5) The rights and obligation given to land development and administration authority hereby transferred to land development and management Burea.

3. <u>የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ህጎች</u>

1. የድሬዳዋ አስተዳደር የአስፈጻሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ሃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣው /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 21/2004 በዚህ አዋጅ ተሽሮአል፡፡

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ደንብ፣መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

4. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በአስተዳደሩ ድሬ ነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ድሬዳዋ ሰኔ 1 ቀን 2007 ዓ/ም**

**አሰድ ዚያድ**

**የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ**

3. **Repealed and in applicable laws**

**1.** a proclamation to amend the definition of powers and duties and re-establisment of the executive and municipal service organs of Dire Dawa Administration proclamation No 21/2011 is here by repealed .

**2.**Any proclamation , regulation, directives or practice which are inconsistent with this proclamation shall be have no effect oon matters provided in this proclamation.

4. **Effective Date**

This proclamation shall enter in to force up on the date of publication in the Dire Negarit Gazeta.

**Done at Dire Dawa this 8th day of June 2015**

**Assed Ziyad**

**Mayor of Dire Dawa Administration**